# ከመጻሕፍት አምባ

የመጽሓፉ ርእስ ...... የወገን ጦር ትዝታዬ
ደራሲ ................ ማሞ ለማ (ሻለቃ)
አሳታሚ .............. ሻማ ቡክስ፣ 2001 ዓ.ም.
አታሚ ................ የተባበሩት አታሚዎች አ.አ. ኢትዮጵያ
የገጹ ብዛት............ 497
ዋጋው ................ ያልተመለከተ
ሂሳዊ ንባብ .......... በአበራ ለማ

## እንደመነሻ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ባገር ቤትም ሆነ በውጭ እየታተሙ የሚወጡ አንዳንድ መጻሕፍት ያንባቢያንን ቀልብ እየሳቡ ነው። ደህና የመወያያ ርእሶችም እየሆኑ ነው። እነዚህ የሕትመት ብርሃንን የታደጉ የቅርብ ጊዜ መጻህፍት ኢልቦለድና ልቦለዶች (Non fiction & fiction) ሲሆኑ፣ ዓይነተኝነታቸው በአራት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል። ይህም ለዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ሂሳዊ ንባብ አቀራረብ ይመች ዘንድ የተመረጠና ሌሎች ሌሎች የሕትመት ሥራ ውጤቶችን (የትምህርት መርጃ መጻህፍትን፣ ሙያ ቀመስ መጻህፍትን፥ ቃለ ተውኔቶችን ወዘተ...) ለጊዜው ያላካተተ መሆኑን ልብ ይሏል።

1. **የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ** (Memoir)
2. **ኔበንተኔና በንተሱ** (እንደ ሰ.መ.* አሰያየም) Autobiography & biography
3. **የታሪክ መጻሕፍት** (History)
4. **የልቦለድና የግጥም ሥራዎች** (Ficton and poetry) **ናቸው።**

ከቁጥር አንድ አስከ ሦስት የተመለከቱት በኢልቦለድና አራተኛው በፈጠራ ሥነ ጽሁፍ ሥራዎች ጎራ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ታትመው ከወጡትና እጄ ከገቡት መካከል፣ ላሠራር ይመቸኝ ዘንድ ጥቂቱን ብቻ በየፈርጃቸው እዚህ ላይ ማመልከትን መርጫለሁ።

**የሕይወት ታሪክ ማስታወቻዎች** ከሚባሉት ውስጥ ...

**ሀ. "አሞራው"** ............... ግደይ ባህሪሹም
**ለ. "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ... ካየሁትና ከሰማሁት** 1896 - 1922"" ... በብላታ መርሴዔ ሃዘን ወልደ ቂርቆስ
**ሐ. "ካየሁት ከማስታውሰው"......** በልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

---

* ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መ. **"አይ ምጽዋ"**........................ በታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ
ሠ. **"መስዋእትነትና ጽናት"**................ በሜ/ጄኔራል ሁሴን አህመድ
ረ. **"ነበር"** (ክፍል አንድና ሁለት) ....... ዘነበ ፈለቀ
ሰ. **"የጋዜጠኛው ማስታወሻ"**.............. በተስፋዬ ገብረ አብ
ሸ. **"የወገን ጦር ትዝታዬ"** ............... በሻለቃ ማሞ ለማ
ቀ. **"የፒያሳ ልጅ"** ........................ በፍቅሩ ኪዳኔ... የሚጠቀሱ ይገኙበታል።

በዚሁ የኢልቦለድ ሥነ ጽሁፍ ጎራ ውስጥ የሚመደብ "የገጠመኝ ጽሁፍ" የሚባለው ክፍል አንድ ሥራም እጄ ገብቶ ተመልክቼዋለሁ። መሃል ሸገር ላይ በታዳጊ ሕጻናቶቻችንና ወጣቶቻችን የሕይወት ኪሳራ ላይ ምን እየተቀመረ እንዳለ ለማየት፣ ወኔውና ትእግስቱ ያለው ሰው፣ የጸሃፊ ደረጀ አያሌውን **"መቃልየ መቃልየ ዘ ቺቺኒያ"**ን ማንበብ ይችላል። ላቅመ ሄዋን ያልደረሰችው የሚጢጢን የመኖር ፍዳና አሳዛኝ ሕልፈት፣ ባንጻሩም ደግሞ ያንዳንድ የዘመኑን ባለሥልጣናት ቅጥ ያጣ ሴሰኝነትና የሲ.ኤም.ሲ.ዎቹን የእንጨት ሽበቶች ቅሌት እስኪያንገሽግሻችሁ ድረስ ትጋታላችሁ። **"ሦስት ባንድ ታውቃለህ?"** እያለች ነበር የነዚህን የምድር ጉዶች የነውር ወሲብ ታሪክ ለደራሲው ያወሳችው።

ሚጢጢ በአሥራ አንድ ዓመቷ እናት አልባ እራሷንና የሦስት ዓመት ሕጻን ታናሽ ወንድሟን ረሃብ ለማስታገስ ስትል ሥጋዋን መሸጥ ተገደደች። በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለመኖር ስትል ስትውተረተር ካያ ሞት ጋር ተፈጣጠመች። "እውነት ይቺ አዲስ አበባ ያቺ እናውቃት የነበረች ከተማችን ናትን?" እያሉ በባይታወርነት ውስጥን መናጥና የቺቺኒያን እምባ የመቅሰፍት ስራዊት የሰፈረባት አድርጎ መራገም አይቀሬ ነው። ግን ግን ይህንን ህዝብ ከንዲህ ዓይነቱ የሥነ ልቡናና የተበላሸ ማህበራዊ ሕይወት ሰለባነት የሚታደገው ማን ነው? ባለቤቱ ማነው? መንግሥት? ፈጣሪ? ወይስ ማን? እያልን ውስጥን መጭነቃችንም የግድ ነው።

ስለ አንድ የኢልቦለድ ሥራ ከመነጋገራችን አስቀድመን ስለ ልዩ ጸባዩ ማወቅ ይኖርብናል። ኢልቦለድ እውነትን እውነት ብሎ የሚያቀርብ የእውነታው ዓለም እማኝ ነው። የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት ሁሉ፣ ቢያንስ ቀጣዮቹ ሦስት ዐቢይ ነጥቦች ትኲረን ይሻሉ።

- *የኢልቦለድ አንባቢያን ከማናቸውም በላይ ደራሲውን ማመን ይፈልጋሉ።*
- *የኢልቦለድ ጹሑፍ እውነት የሆነውን ነገር ወክሎ መቅረብ ይኖርበታል።*
- *የኢልቦለድ ጽሑፍ አቀራረብ ተአማኒነትን ለማጎልበት ፋይዳው ማድረግ ይጠበቅበታል።*

በዚህ መመዘኛ ረገድ ሚዛን የሚደፋና ያንባቢን ቀልብ ከሚገዙ የቅርብ ዓመታት ሥራዎች መካከል ብዙዎቹን በናሙናነት ወስዶ መፈተሽ ይቻላል። ሆኖም የዚህ ጽሁፍ ዋና ትኩረት ይህ ባለመሆኑ፣ ጉዳዩን ብቻ ጠቁሞ፣ ወደ አቢይ ፋይዳው ማለፍን ጸሃፊው መርጧል።

በኢልቦለድ ሥራዎች የትናንት ትናንትን ለዛና ጣእም ለማጣጣም፣ ዛሬን አድምቆ ለማየትና መጻኢ ወደፊትን ለማጮለቅ እነኚህን ዓይነት ተጠቃሽ መጻህፍት ላይነ ንባብ ማብቃቱ ብርቱ ጠቀሜታ አለው። ለምሳሌ እንደ አንጋፋው ደራሲና ጋዜጠኛ እንደ ብላታ መርስዔ ሃዘን ሥራ የመሳሰለው ትናንትን እንደ ብሩህ መስታወት አጥርቶ የሚያሳይ ነው።

አንጋፋው የቋንቋና የሥነ ጽሁፍ ሰው ብላታ መርስዔ ሃዘን ወልደ ቂርቆስን የማያስታውስ የኛ ዘመንተኛ ይኖራል ብዬ አልገምትም። "የአማርኛ ሰዋሰው" በሚባለው ብቸኛ የቋንቋ ሥርዓትና አገባብ መማሪያ መጽሃፋቸው አሳምረን እናስታውሳቸዋለን። ብላታ አሥራ ሁለት ወጥ ጥናታዊና ትምህርታዊ መጻህፍትን ከመድረሳቸውም ባሻገር (የታተሙ)፣ ሰባት የትርጉም ሥራንም ላይነ ንባብ አብቅተዋል። ከሌሎች ምሁራን ጋርም ስምንት ሥራዎችን አበርክተዋል። ያልታተሙ ስድስት ወጥ ሥራዎችም እንዳሏቸው ልጃቸው አምሃ መርስዔ ሃዘን በቅርቡ ባሳተሙላቸው



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ያባታቸው መጽሃፍ መግቢያ ላይ አስታውሰውናል። ብላታ መርስዔ ሃዘን በ1964 ዓ.ም. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነጽሁፍ ተሸላሚም ነበሩ።

ብላታ መርስዔ ሃዘን የተዋጣላቸው የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ ጸሃፊ እንደ ነበሩ፣ እነዚህ ሦስት ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ይዞ ሥራቸውን መፈተሽና እርካታን ማግኘት ይቻላል።

- የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ ሌሎች እንዲያነቡት የሚጻፍ ነው።
- የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ አንባቢውን ከግንዛቤው ውስጥ ከቶ የሚዘልቅ ነው።
- የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ ከተነባቢነት ፋይዳ ጋር ቁርኝት ያለው መሆን ይኖርበታል።

ይህ ልጃቸው አቶ አምሃ በቅርቡ ያሳተሙላቸው "የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ... ካየሁትና ከሰማሁት 1896 - 1922" መጽሃፋቸው ውስጥ አያሌ ድንቅ ትዝታዎቻቸውን ጥለውልን አልፈዋል። ውብ በሆነ የሥነ ጽሁፍ ቋንቋ አተራረክ፤ በዚያን ዘመን የነበረውን እውነተኛ ገጽታ እንደ ፎቶ ሽመልስ (እውቁን የ50ና የ60ዎቹን አሥርት ዝነኛ የሸገር ፎቶግራፍ አንሺ ሽመልስ ደስታን ያስታውሷል) የካሜራ ጥበብ ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። ስለ ብላታ ሥራዎች በጣም ብዙ ብዙ ሊባል ይቻላል።

**ኔበንተኔ** ከሚባሉት ውስጥ ...

ሀ. **"ኦቶባዮግራፊ"................** በፊታውራሪ ተክለ ሃዋሪያት ተክለ ማርያም
ለ. **"አንድ አፍታ ላውጋችሁ"**..... በፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ
ሐ. **"የጦር ሜዳ ውሎ"**........... በብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተ ማርያም
መ. **"የጦር ሜዳ ውሎዎች፣ ከምሥራቅ እስከ ሰሜን** (Autobiography)... በብ/ጄ. ካሣዬ ጨመዳ
ሠ. **የጨለማ ሌላኛው ገጽታ፥** የቄስ ጊዳዳ ሶለን ግለታሪክ.... በግርማዊ ቡሽን (ትርጉም)... ይካተታሉ።

በዚህ ጎራ ውስጥ የተካተቱትን ዓይነት ኔበንተኔዎችን ማንበብም የጸሃፊዎቹን ተክለ ሰብእና በጥልቀት ለማየት ያመቻል። ትውልዳቸውን፥ አስተዳደጋቸውን፥ ትምህርታቸውን፥ ሥራቸውን፥ ባገራቸው ውስጥ የነበራቸውን ሚናና ሰፊ ልምዳቸውን ለመቃኘት ያስችላል። ላይነት ያህል የፊታውራሪ ተክለ ሃዋርያትን ኦቶባዮግራፊ ያናገረ እንኳን ብዙ ብዙ ጠቃሚ ነገርን ይገበይበታል።

የፊታውራሪ ተክለ ሃዋሪያትን ዓይነት ሥራ ሁሌም ለቁም ነገሩና ለተክሌ ግለኛ ሰብእና ስንል እየተመላለስን ብናነበው አንጠግበውም። ይህ ሥራቸው ከቋንቋ አጠቃቀማቸው፣ ከሃሳብ አሰዳደር ክሂላቸውና ካመለካከታቸው አንጻር የነዘመነ ቶልስቶይ መልካም ደቀ መዝሙር መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል። የኮንስቲትዩሽንን አስፈላጊነት የሚረዳላቸው ባለጊዜ ለማግኘት እንደዲዮጋን በቀተረ ተሲዓት ኩራዝ ለኩሰው ሲንከራተቱ ማስተዋል ውስጥን ይበላል። ከራሻዊቷ "አያታቸው" በተማሩትና ባስተዋሉት መሰረት የባለ ብዙ ጋሻ መሬት ባለእርስትና ባለጉልጥምት በመሆን፣ ሰፋፊ ሁዳዶቻቸውን እያሳረሱ የመኖር ሕልማቸውንና ስኬታቸውን ስናጤን፤ ዘመናቸው፥ ትምህርት ቤታቸውና ያደጉበት ሥርዓት የቀረጻቸው ሞዴል ለመሆናቸው እማኝ መቁጠር አያስፈልግም። ለራስ ተፈሪ መኮንን የተሰጠው ዓይነት አንድ ምላሽ ሁሌም አይረሴነት ያለው ነው። ምልልሱ እንዲህ ይመስላል....

"አዲስ ያቀናኸውን ከተማ ስም "አስበ ተፈሪ" ብለህ እንድትሰይመው..." ራስ ተፈሪ መኮንን።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

“አልሰይምም። አንተ እራስህ ያቀናህውን ከተማ እንደሱ ብለህ ሰይመው” ፊታውራሪ ተክለ ሃዋሪያት።

“እንድትሰይመው አዝዤሃለሁ!... ትእዛዝ ነው!...” ራስ ተፈሪ መኮንን።

እንዲህ መሰሉ እውነት፥ እልክና ሥልጣን የሰውን ልጅ ማንነት የሚፈርጁበትን አጋጣሚዎች ስናነብ የምጸት ፈገግታ ማሳየታችን አይቀርም። ተክሌ ላሻፈረኝ ባይ የመሬ ልጅ ባህሪያቸው የእግረ ሙቅ ሰለባነት እዳ ከፍለውበታል።

በሌላም በኩል ተክሌ ያንን ሁሉ እርስት ከበር በመለስ የማግበስበስ አባዜያቸው ምን ጊዜም የማይበርድ በመሆኑ፣ በመጨረሻው በነገረ ሠሪዎች አቤቱታ ራስ ተፈሪ፣ “ከዛሬ ጀምሮ እኔን ሳታስፈቅድ ምንም ዓይነት እርስት እንዳትገዛ!...” ብለው ያስተላለፉባቸው መመሪያ አንባቢን ያስገርማል። እናም ሊዮ ቶልስቶይ ባንዲት የኖቭሌት ሥራው ላይ **“ላንድ ሰው ምን ያህል መሬት ይበቃዋል?”** ሲል በምጸት ያቀለመውን ታሪክ ተክሌ ያሳታወሱት አይመስልም።

እንግዲህ እንዲህ እንዲህ እያልን ብዙ ብዙ እንደሃረግ እየመዘዝን፣ የምናወሳው የዚህ ሽጋ ሥራ አንጓ ሞልቷል። ለምሳሌም ያህል ከግርጌ የተመለከተውን ከመጽሃፉ የቀነጠብኩትን ጥቅስ እንደምን እንምለከተዋለን? የሚል ጥያቄዬን ለትሁት አንባቢያን ማቅረብን እሻለሁ። እውን ያለመግባባት ፈሊጣችን መንስዔው ተክሌ እንዳሉት ሁሉ ቅይጥ መሆናችን ይሆን? እናም ይህ መቀየጣችን እስከመቼስ እንደባእድ የጎሪጥ እያስተያየን ይኖር ይሆን? ላለመስማማትስ እየተስማማን መኖር እስከመቼ፥ ምቾትና ውስጣዊ ሰላም ይሰጠን ይሆን? ፊታውራሪ ተክለ ሐዋሪያት እንዲህ ይሉናል...

“”ይልቅስ ሕዝቡ ስህተት የበዛበት ነው። እንደዚህም የሆነበት ምክንያት ታውቀዋል። ካንድ ጅንስ (ዘር) ያልመጣ ቅይጥ በመሆኑ ነው። ለዚህም ምክንያት የሆነው ያገራችን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ከስሩ አያይዘን ጠብቀን ስንመለከተው፤ በየጊዜው ጉዳት የሚደርስበት በጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ መሆኑ በግልጽ ይታያል....” (ገጽ 158)

## **የታሪክ መጻህፍት** ከሚባሉት ውስጥ...

- ሀ. **“የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል”** ... በብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ ሥላሴ
- ለ. **“ክህደት በደም መሬት”**...................... በሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ
- ሐ. **“የኢትዮጵያ ታሪክ (ከ1847= 1983)”** .. ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ
- መ. **“የአናብስት ምድር”**......................... በታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ
- ሠ. **“ የ1953ቱ የመንግሥት ግልበጣ መከራና ከ1908 = 1966 የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት”**..................... በኮ/ል ቃለ ክርስቶስ አባይ
- ረ. **“ምስክርነት በባለሥልጣናቱ አንደበት”** ...... በሻምበል ተሰፋዬ ርስቴ
- ሰ. **“ለኢትዮጵያ ታሪኳ ነው መልኳ”**............. በአፈሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ...

ይጠቀሳሉ።

በዚህ ዘርፍ ውስጥ የተካተቱት ታሪክ ቀመስ ሥራዎች ሁለት ዓይነት ያጻጻፍ ገጽታ ያላቸው ናቸው። አንዳንዱ የታሪክ ጽሁፍን አጻጻፍ ወግ ተከትሎ በግርጌ ማስታወሻና በዋቤ መጻህፍት አጠቃቀስና አጠቃቀም ረገድ የተዋጣ አቀራረብን የተካነ ነው። አንዳንዱ ደሞ ካንጻር ምርጫው ጀምሮ የትኛውን ይዞ የትኛውን ትቶ የታሪክ ጽሁፉን ለገጸ ንባብ እንደሚያበቃ ግራ የገባው የሚመስል ነው። የግርጌ ማስታወሻ አጠቃቀሙም፥ የዋቤ መጻህፍት አጠቃቀሱም ሁሉ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ውንግርግሩ የወጣበት ሆኖ ይስተዋላል። ከዚህ ከሁለተኛው ዓይነት የተበላሸ ያጻጻፍ ቴክኒክ የምናገኘውም አላባ እንደዚያው የተምታታና እናትዋን እንዳጣች ግልገል የሚዋልል ዓይነት ሆኖ እናገኘዋለን። ካነበብኳቸውና ካልተዋጣላቸው የታሪክ መጻህፍቱ ዝርዝር ውስጥ የሻምበል ተስፍዬ ርስቴን "ምስክርነት" ላብነት መጥቀስ ይቻላል።

የሻምበል ተስፋዬ ሥራ የባለ ሙያ እገዛ የተነፈገውና ወርቅ የሆነ ጥሬ ነገርን (material) በወጉ መጠቀም ያልቻለ መካን ሥራ ነው። በጭብጥ ደረጃ የሚያነሳቸውን ፍሬ ነገሮች፣ በታሪክ ጽሁፍ አጻጻፍ ቴክኒክና በታሪክ ቋንቋ አጠቃቀም ድክመት ምክንያት ሥራውን ሊዳጨው ችሏል። አንዳንድ ቦታ ላይ የሚያነሳቸውን ብርቱ ጉዳዮች መግለጽ ሲያቅተው፣ የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ብይኖችን ሰጥቶ ሲያልፍ ይስተዋላል። ደርግን ከዚያ ሁሉ የሥልጣን ጥማትና አምባ ገነናዊ አመራር ነጻ ሊያዋጣ ሲፈልግ፣ ጦሱን ሁሉ ለነመኢሶንና ኢሕአፓ ሰጥቶ ቁጭ ይላል።

የደርግ አስቀያሚው ገጽታ ባለቤቶች ሁሉ እነዚህን ድርጅቶች የመሳሰሉ እንደሆኑ ሰበብ እያፈላለጉ ሲዳርጉባቸው ይስተዋላሉ። "... የኢትዮጵያ ምሁራን... ሁሉን የሚጠሉ ናቸው። ባህላቸውን፣ ኢትዮጵያዊነትን ይጠላሉ፣ ይንቃሉ። ሁሉን ማፍረስ ይወዳሉ... እርስ በርስ መተማመን፥ መደጋገፍና መረዳዳት ሳይችሉ ቀርተዋል። (ኢሕአፓና መኢሶን በአብዮቱ ወቅት የሠሩትን ያጤኗል) የጥቅም ሥስታም ናቸው። የሥልጣን ስስታም ናቸው። ጨካኞች ናቸው..."" (ገጽ 115) እያሉ እንዲህ ያዘናጉናል። ደርግን ሳይሆን እኒህ የወደቀ ዛፍ ተምሳሌቶችን በሁሉም ረገድ እንድንረባረብባቸው ይወተውቱናል።

እኚህ ጸሃፊ አንድ ነገር ግን ዘነጉ። እሳቸው እንደሚሉን በኢሕአፓና በመኢሶን ክፋትና ጨካኝነት አንጻር፣ እርሳቸውና እርሳቸው የሚያሸሞነሙኑት የወታደራዊው ደርግ አመራር የትኛውን የስልጣን ቸርነትና ርህራሄ እንዳደረጉ ሹክ ሳይሉን ማለፋቸው ነው። ወይም ወይም አሁን የሚኖሩበትን የወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት የሥልጣን ቸርነትና ርህራሄ ላብነት ያህል ወዲህ ቢያቀብሉን መልካም በተደረሰናቸው ነበር። ስለወያኔ/ኢሕአዴግማ አንዲት ዘለላ መስመርም ሳይጭሩ የብእር ቀለማቸው ነጥፏል። ምናልባት በቀጣዩ "የታሪክ" ጹፋቸው፣ ሊያስነብቡን የይደር ቀጠሮ ይዘውልን ይሆናል።

ባጠቃላዩም ይህ ሥራቸው ሲመዘን፤ የመልካም ኢልቦለድ ጽሑፍን ደረጃ የማያሟላና ከማሳየት ይልቅ በመናገር ላይ ያተኮረ ረጋ ሠራሽ ሥራ ነው። ያማርኛ ቋንቋን የጻጻፍ ህግም በብርቱው የሚጻረሩ ችግሮችም ተስተውለዋል። ረዣዥም አረፍተ ነገሮችን መጠቀም፥ አንዳንድ ቃላትን ያለ ስፍራቸው መሰንቀር፥ አንቀጾችን አለመመጠን ይስተዋላል። ይህም ላንድ የኢልቦለድ ሥራ የተነባቢነቱን ፍጆታ በመቀነሱ ረገድ፣ አፍራሽ ሚናን እንደሚጫወት መጠቀምን እንወዳለን።

**የልቦለድና የግጥም ሥራዎች** ውስጥ...

ሀ. **"ቢስ ገላ"**............................... በፀሐይ መልአኩ
ለ. **"ቅበላ"ና ሌሎችም**....................... በአለማየሁ ገላጋይ
ሐ. **"ዳርቶጋዳ"**............................... በይስማዕከ ወርቁ
መ. **"ግራጫ ቃጭሎች"**..................... በአዳም ረታ...
ሠ. **"ከጥቁር ሰማይ ስር"** እና ሌሎችም.... በእንዳለ ጌታ ከበደ
ረ. **"ኗሪ አልባ ጎጆዎች"** እና ሌሎችም.... በእውቀቱ ሥዩም
ሰ. **ልጅነት**............................... በዘነበ ወላ የመሳሰሉት ላብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በዚህ በልቦለዱ ዘርፍ አንድ አዲስ ያልተለመደ ዓይነተኛ ሥራ ሆኖ የብዙ አንባቢያንን ቀልብ በቅርቡ የሳበው፣ የይስማዕከ ወርቁ "ዳርቶጋዳ" ነው። ከሳይንስ ልቦለድ (Science fiction)




PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አጻጻፍ ጎራ የሚመደብና ላይነትም በብርቱ የሚጠቀስ ነው። በጥሩ የሥነ ጽሁፍና የሥነ ሕይወት ሙያዊ ቃላት የሸገነ ሥራ ነው። አንባቢን ወጣሪና ከእውነታው ዓለም ጋር እያፋለመና እያዋዛ ጣናን የሚያስቀዝፍ ነው።

እነዚህ ለዓይነት ያህል የተጠቀሱትም ሆኑ ሌሎቹ አዳዲስ የወጡ አብዛኞቹ መጻህፍት ብዙ ሊባልላቸውና ሂሳዊ ንባብም ሊካሄድባቸው የሚገቡ ናቸው። በዚህ ዓይነት አንድ አቢይ ጉዳይን ለማየት በተመረጠ ርእስ ስር ስለሁሉም ብዙ ለማለት ባይቻልም፣ በሌላ ጊዜ ተመልሶ በሌሎቹም ተጠቃሽ ሥራዎች ላይ ሊጻፍባቸው እንደሚችል የዚህ መጣጥፍ አቅራቢ ያምናል። እናም ለዛሬው ትኩረቴ ወደ መረጥኩት የሻለቃ ማሞ ለማ "የወገን ጦር ትዝታዬ" ሥራ ላቅና።

# "የወገን ጦር ትዝታዬ"



"የወገን ጦር ትዝታዬ" ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ፣ በኢልቦለድ የሥነ ጽሁፍ ጎራ፣ በሕይወት ታሪክ ማስታወሻ አጻጻፍ ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው። ከኤበንተኔ አጻጻፍ የሚለየው፣ ደራሲው የራሱን የትወልድም ሆነ የእድገት ወዘተ... ጉዳይ ፋይዳዬ ብሎ አንስቶ ከሀ እስከ ፐ ድረስ አለመተረኩ ነው። የ "ኤበንተኔ" ጸሃፊ ከልደት እስከ... ዓይነት ትረካን በራሱ የሕይወት ታሪክና ገጠመኝ ዙሪያ ያጠነጥናል። "የወገን ጦር ትዝታዬ" ዓይነቱ የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ ጸሃፊ ግን፣ ከሕይወት ዘመኑ አንድ አንጓ እውነትና እውነት የሆነ ገጠመኝ በመነሳት፣ በዚያ መቼት ዙሪያ ያጠነጠነውን ማስታወሻውን ያስነብባል። እናም በዚህ አግባብና አንድምታም ነው የሻለቃ ማሞን ሥራ የምንቃኘው።

ሻለቃ ማሞ የረዥም ጊዜ ልምዳቸው የዘመቻ መኮንንነት ባጠቃላይም ውትድርና እንጂ ጸሃፊነት አይደለም ብሎ እሰጥ አገባ የሚሄድ ሁሉ፣ ይህን ሥራቸውን ካነበበ በኋላ መረታቱ አይቀሬ ነው። ሰውዬው ባንድ እጃቸው ክላሽንኮቭ በሌላኛው እጃቸው ደሞ ብእር ጨብጠው የኖሩ ዓይነት ሰው ነው... ሥራቸው የሚያስመሰላቸው። ሃሳባቸውን በወጉ አፍታተው መግለጽ የሚያስችላቸው ሁለንተናዊ የቋንቋ ችሎታቸውና ጉልበታቸው የሚደነቅ ነው። የኢልቦለድ ሥራ ማቅረቢያ ቋንቋቸውና የወታደራዊ ሙያቸው ቋንቋ ብቃትና የሁለቱ ተጣጥሞሽ ለሥራቸው ስኬት ትልቁን አስተዋጽኦ እንዳደረገላቸው ማስተዋል አያዳግትም። በርግጥ አልፎ አልፎ በአርታዒ እጅ ሊቃኑ ይችሉ የነበሩ ያንቀጽ አቀማመጥ ስህተቶች ይስተዋላሉ። "አንድ አረፍተ ነገር አንድ አንቀጽ ሆኖ አይቀመጥም" የሚለውን ያማርኛ ቋንቋ ያጻጻፍ ሕግ ይጻረራልና ነው ይህን ማለታችን።

ሌሎቹም በጦር ግምባር ዙሪያ የተጻፉ አንዳንድ መጻህፍት የየበኩላቸውን ያተራረክና የመግለጽ ብቃት ማሳየታቸውን አሌ ማለት አይቻልም። ታደሰ ቴሌ ሰልቫኖ፥ ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሃብተ ማርያምና ብ/ጄኔራል ካሳዬ ጨመዳ ብርቱ ሥራዎች ካቀረቡልን ጸሃፍት መካከል ናቸው። ያንን ዘግናኝ የምጽዋ እልቂት ታደሰ ቴሌ እንደ ካሜራ ቀርጸው አስይተውናል። ጀነራል ተስፋዬ የናቅፋን አስደናቂ ግዳጅ አውጣጣቸውን፥ ጄኔራል ካሣዬ የጅጅጋውንና ባጠቃላይም ከወራሪው የዚያድ ባሬ ጦር ጋር የተደረገውን እልክ አስጨራሽ ፍልሚያ በየበኩላቸው እንደመስታወት አሳይተውናል። ይሁንምና ሻለቃ ማሞ የጦር ግምባር ሁለንተናዊ ገጽታንና ሕይወትን በላቀ ደረጃ ባማርኛ ቋንቋ ፍንተው አድርገው ማሳዬት በመቻላቸው፣ ካድናቆቱ ያንበሳውን ድርሻ ሳይወስዱ አይቀሩም የሚል እምነት አለኝ። ይህ ሥራ እውነታን መደላድሉ አድርጎ፣ በሚዛናዊ አቀራረቡ ከበላይ አካል እስከ ተራ ወታደሩ ያለውን መዋቅር ሁሉ በወታደራዊ ሙያ ግብአት አኳያ የሚያሄስ ነው። ሻለቃ ማሞ ችግርን ብቻ የሚነግሩን ሳይሆኑ፣ የችግሩን አፈጣጠር መሠረት እየመረመሩ መፍትሄውንና አማራጩን ሁሉ እየጠቆሙ በማሳዬት ነው... ጠንከር የሚሉብን።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ለኢልቦለድ ጸሃፍት አንድ ትሁት የባለሙያዎች ምክር አለ። ይሄውም...

- *ያጻጻፍ ውበት ያለው የኢልቦለድ ሥራ ማቅረብ ከፈለክ፥ በልቦለድ አጻጻፍ ጥበብ ለመካን ተጣጣር።*
- *ኢልቦለዳዊ የፈጠራ ሥራ ምንጊዜም እውነትነቱን እንደጠበቀ መቆየት አለበት።*
- *በኢልቦለዳዊ የፈጠራ ሥራሀ፥ አሳይ እንጂ እንዳትናገር፣....* የሚሉ ናቸው

ይህን ምክር ሻለቃ ማሞ በወጉ የተጠቀሙበት ይመስላሉ። ጸሃፊው ጦር ሜዳን እንደ መልካም የእጅ መዳፍ አንባቢ ጠበብት አብጠርጥረው አንጠርጠረው ያስነብቡናል። ያሳዩናል። ወይንም በዘመቻ መኮንንነት ዘመናቸው ከጃቸው እንደማይለያቸው የጦር ሜዳ ካርታቸው ንባብ ሁሉ፣ የትናንት ውሏቸውን በቃላት እያሰሱ እኛን ያስንብቡናል። ሰማዩ፥ ተራራው፥ ኮረብታው፥ ከተማው፥ መንደሩ፥ ሸለቆው፥ ሸንተረሩ፥ ጉራንጉሩ፥ ሰርጡ፥ ጉድባው፥ ወንዙ፥ ኩሬው፥ ምንጩ፥ አሸዋው፥ አለቱ.... መልክአ ምድሩ ሁሉ በያይነት በያይነቱ ሲገለጥልንና፣ የሰው ልጅ በነዚህ ሁሉ ውስጥ በእሳት እየተፈተነ ሲያልፍ ወይም ሲያሸልብ እንደሲኒማ ያሳዩናል። ባኳያውም ጀቱ፥ ታንኩ፥ ብረት ለበሱ፥ መድፉ (120 ጀነራል መድፍ፥ ግራርፒ፥ 80፥ 70 ሚ.ሜ. ወዘተ...)፥ መትረየሱ፥ አር ፒ ጂው፥ ዶሽቃው፥ ዙ 23፥ ቦምቡ፥ በያይነት ጠመንጃው.... ይነገረናል ሳይሆን፣ ይስተዋለናል። በነዚህም አረርና የሳት ላንቃ እዚያም ቤት እዚህም ቤት ሕይወት ስትበላ፥ ሕይወት ስትጠጣ ሸጋው ብእረኛ ያሳዩናል።

በሕይወት ታሪክ ማስታወሻ ጸሃፊነታቸውም ሻለቃ ማሞ በኤርትራ በረሃዎች ውስጥ እጅግ ፈታኝ በሆኑት ያልጌና፥ ያፋቤትና የሌሎችም ጦር ሜዳዎች ላይ ያሳለፏቸውን የጀግንነት፥ የሞትና የሽረት ወቅቶች (ክፉ ዓመታት፥ ወራት፥ ቀናት፥ ሰዓታት፥ ደቂቃዎችና ቅጽበታት...) ሁሉ እንደ ደህና ካሜራ ቀርጸው ለተደራሲያን አካፍለውናል።

ከብዙ ብዙ ክፉ ገጠመኞቻቸውም መሃል እንዲህ እንዲህ ያለው ይጠቀሳል።

> "...አንድ ወታደር በዝግታ ወደሚሄደው ኡራል መኪና ሮጥ ሮጥ ብሎ ተጠጋና ከነጂው ጋር እንደመነጋገር ብሎ የመኪናውን መዝጊያ ይዞ በመንጠልጠል ከነጂው አንድ ነገር ይቀበላል። ያን መከረኛ ሲጋራ ይሆናል.. ምድር ያደበላለቀ ፍንዳታ ሰማሁ። ዓይኔን እዚያ አየው የነበረ መኪና ላይ ስወረውር መኪናው በጥቁር ጭስ ተሸፍኗል። ከጭሱ በላይ ወታደራዊ (ፊልድ) ጃኬት ... ወደ ሰማይ ተወርውሮ እንደገና ይወርዳል... ወደ ተመታው መኪና ሮጬ ስሄድ... ነጂው አላንዳች ጉዳት አምልጧል።
>
> "ሌላስ ሰው ተርፏል?" ብዬ ጠየቅኩ።
>
> ነጂው ራሱን ይዞ "እኔ ደህና ነኝ። ፈንጂው በሙሉ እሱ ላይ ነው ያረፈው" አለኝ።
>
> ".. ያ ለካስ እንደቅጠልና እንደ ወረቀት ባየር ላይ ይንገዋለል የነበረው ጃኬት ቀደም ሲል የመኪናው በር ላይ ተንጠልትሎ የነበረ ወጣት ኖሯል። ዓይናችን እያየ አካሉ ተበጣጥሶ ባካባቢው ላይ ተዘራ። የሰው ልጅ ሕልውና እንዲህ በቅጽበት እንዳልነበረ ሆኖ ከትቢያ የሚደባለቅ ዘግናኝ ነገር ሆኖ ይቀራል።"" (ገጽ 206 - 207)

ጸሃፊው የዚህ ዓይነቱን ቅጽበታዊ የሰው ልጅ ሕይወት ቅጥፈት በተለያዩ የጦር ሜዳዎች ላይ በተናጣልም በጅምላም አስተውለዋል። ይህ ከለጋ እድሜያቸው ጀምሮ አብሯቸው ያደገ እጣ ፈንታ ዛሬም ያ ክፉ ትዝታው ከውስጣቸው አልወጣ ብሎ እንደሚያስቃያቸው በየምእራፎቹ ላይ እየተዘገነኑ ገልጸውታል። በተለይም እጅግ በጀግንነቱ የሚያደንቁትና የሚወዱት ጓደኛቸው



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመቶ አለቃ ተስፋዬ አያና፣ ሥርአት አልበኛና አምባገነን በሆኑ አዛዦች፥ ካድሬዎችና ተከታዮቻቸው ደባ አዚያው ጦር ግምባር ላይ እንዲረሸን መደረጉ እንደ እግር እሳት ሲያቃጥላቸው መኖሩን አምርረው ይገልጻሉ።

“...ርሸናው በጠዋት መካሄዱንና ሃያ ሁለቱ ሰዎች መገደላቸውን ተስፋዬም... ከሌሎች የ324ኛ ሻለቃ አባላት ጋር መገደሉን ነገረኝ... በዚህ ዓይነት የገዛ ወገናችንን እያረድን በየሜዳው እየጣልን የትኛው ውጊያ ሊቀናን? ... እግዚአብሄር የለም ማለት ነው እያልኩ ፈጣሪዬን የማማርርበት ደረጃ ደርስኩ... ሁላችንንም እንደኖህ ዘመን ያለ የጥፋት ውሃ አጥለቅልቆ እንዲጨርሰን ተመኘሁ። ባንድ ጊዜ ጠባዬ ሁሉ ተለውጦ ሌላ ሰው ሆንኩ። በረዥም የጦር ሜዳ አገልግሎቴ ብዙ የከፋ ውጊያ ስቃይና መከራ አሳልፌያለሁ። እንደዚያ ጊዜ ግን መንፈሴን የመረዘ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም።” (ገጽ 119/120) እያሉ በውስጣቸው የነበረውን ጽኑ መከፋት ገልጸውታል።

በዚህ የራስን ወገን በራስ እጅ የመብላት ያልጌና ግምባሩ ክፉ ድርጊት፣ ከያንዳንዱ ብርጌድ ሃያ ሃያ ሰው፥ ከልዩ ልዩ ክፍሎች ደሞ ከመቶ ሰው በላይ ጭዳ እንደተደረገ ይተርካሉ ሻለቃ ማሞ። ይህ ሁሉ አሳዛኝ ድርጊት የተፈጸመው የበላዮች የሰጡትን የተሳሳተ የውጊያ አፈጻጸም ስልትና የተከተለውን ከፍተኛ ውድቀት፣ በምስኪን መስመራዊ መኮንኖች፥ የበታች ባለሌላ ማእርጎችና ተራ ወታደሮች ቅጣት ሽፋፍኖ ከተጠያቂነት እራስን ለማዳን ነበር።

ጸሃፊው ቀደም ብለውም ባወሱት አንድ አሳዛኝ ገጠመኝ ላይ እንዲህ የሚል ይነበባል። የመቶ አለቃ ጌታቸው ደምሴ የሚባል አንድ የመረጃ መኮንን ግዳጅ ላይ ፈጽሟል በተባለው የአፈጻጸም ስህተት በማርሻል ኮርት እንዲረሸን ይወሰንበታል። ውሳኔውን በበላይነት የሰጡት ጀኔራል አበራ አበበና ኮሚቴያቸው ነው። ሆኖም ከብርጌድ አዛዡ ከሻለቃ መረሳ የይሁንታ ምላሽ እስካልተሰጠ ድረስ ተፈጻሚ ሊሆን ስለማይችል ችኩሉና ጨካኙ ጀነራል አበራ ሻለቃ መረሳን ለስምምነቱ አጥብቀው ይጠይቋቸዋል። ቆራጡ ሻለቃ መልሳቸው አጭር ነበር። “ ጌታዬ፣ እንኳን እስረኛውን መኮንን እኔንም ቢሆን የማስገደልና የፈለጉትን ማድረግ የሚያስችል ሥልጣን ስላለዎት የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ እንጂ ከማውቀውና ከማምንበት ውጭ በትእዛዝና በጫና ሰው ይገደል ብዬ አስተያየት አልሰጥም” ማለታቸውን በእማኝነታቸው የሰሙትንና ያስተዋሉትን አስፍረዋል።

ደራሲው፣ ያንዳንድ ብርቱ ጀግኖቻችንንም ተጋድሎና ሕልፈት ለዓይነት ያህል አልፎ አልፎ በየምእራፎቻቸው ውስጥ እንደጌጥ ጣል ጣል እያደረጉ ያተራረክ ስልታቸውን አጓጊና ጣፋጭ አድርገውታል። የጀግናውን፥ ያስተዋዩንና የቆራጡን የሻለቃ መረሳን ድንቅ የጦር ሜዳ ውሎ ያነሱባቸው ገጾች ብዙ ናቸው። በአልጌና ግምባር ለአምስት ዓመታት በበረሃ ሲጠበስ በቆየው ሠራዊት ውስጥ፣ የብርጌድ አዛዥ ሆነው ብዙ የጀግነንት ተግባሮችን የፈጸሙት የሻለቃ መረሳ ፍጻሜ የብዙዎችን ልብ የሰበረና ቆራጥነትን ያስጠየቀ ነበር ሲሉ ጸሃፊው ያስታውሳሉ።

ሻለቃ መረሳ ብዙ ግዳጆች ላይ ሲውሉ ብዙ ያሟሟት አይነቶችን ሁሉ እየናቁ፥ ሞትና እሳቸው ከቶም ሊተዋወቁ እንደማይችሉ በልበ ሙሉነት እየተናገሩ ለጦሩ ሁሉ በጀግንነታቸው አርአያ እንደነበሩ ይህ መጽሃፍ ያወሳል። በተለይም ፈንጂ የሚባል ነገር ከቶም ሊደፍረኝ አይችልም የሚሉና የፈንጂ አደጋ ደምበኞች የሆኑትን እነ ሻለቃ ማሞን ያሾፉባቸው እንደነበር ተተርኳል።

ከ1971 እስከ 1976 ዓ.ም. ድረስ ፈታኝ ፍልሚያዎች ባልጌና ግምባር ሲካሄድ ቆይቶ፣ በመጨረሻው ላይ የጦሩ አቅም እየሳሳ መሄዱን ያወቀው ሻቢያ መጠነ ሰፊ ማጥቃት ሲሰነዝር ጦሩ የመፈታት መጥፎ እጣ ፈንታ ገጠመው። በዚህ ውጊያ ላይ ጠላት እየገፋ መጥቶ የወገን ጦር እሩብ ያህሉ ብቻ ማፈግፈግ ሲችል፤ የቀረው በሞትና በምርኮ ከጥቅም ውጭ ይሆናል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መቀመጫውን አዲስ አበባ ላይ ያደረገው የበላይ አካል አስቀድሞውኑንም ለጦሩ የክፉ ጊዜ ጥንቃቄና ዝግጅት ባለማድረጉ የሚደርስለት አጥቶ እንደወጣ ቀረ።

ሩብ ያህሉ ጦር በማፈግፈጉ ሂደት ላይ እያለ ጠላት የወገንን ድርጅት ይከብና የጅ በጅ የጨበጣ ውጊያው ይፋፋማል። ወዲያውም ከታንክ ጋር ግብግብ ይገጠማል፡፡ ሻለቃ መረሳ አጠቃላይ የጦርነቱ አካሄድና የደረሰበት ደርጃ ክፉኛ ያበሳጫቸዋል። እናም እራሳቸውን ለማጥፋት ሲሞክሩ ተረባርበው ጓደኞቻቸው ያስጥሏቸዋል። ግና ውስጣቸው በጠላት እብሪትና በበላይ አካላት ደባ የነፈረው ቆራጡ መረሳ ከመጨረሻው ውሳኔያቸው የሚናጠቡ አልነበሩም። ዙሪያቸውን የከበቡዋቸውን ውድ የትግል ጓደቻቸውን አዘናግተው አንድ ቅጽበታዊ እርምጃ በራሳቸው ላይ የወሰዳሉ፡፡ የማጥቂያ የእጅ ቦምባቸውን ከመቅጽበት ከመጠበቂያው ይነቅሉና እላዩ ላይ ተኝተው አሰቃቂ ሞት ይሞታሉ።

ጸሃፊው ሻለቃ ማሞ ስለ እኚህ አለቃቸው እንዲህ ይላሉ። “… እርሱ ግን በተመኘው ዓይነት ነው የመጨረሻ እንቅልፉን ያንቀላፋው። ሻለቃ መረሳ ሁልጊዜ የሚላትንና የሚመኛትን ነው ያደረገው። ሻለቃ መረሳ ልበ ሙሉ ጀግና ከመሆኑም በላይ በሃገሩና በወገኑ ላይ ጥቃት ሲደርስ ማየትና ለጠላት መሸሽን በፍጹም አይወድም ነበር። ከዚህ ሞትን ይመርጣል። ውርደትን እንጂ ሞትን አይፈራም ነበር….። (ገጽ 50)

ጸሃፊው አንድ የውጊያ ውሎ ለወገን ጦር ያልተመቸና ጠላት ከባድ ጉዳት ያደረሰበት ሁኔታ ከገጠመ፣ እንደ አልጌናው ግምባር ፍጻሜ ሁሉ ለጠላት እጅን ላለመስጠት ሲሉ እራሳቸውን በራሳቸው የሚያጠፉ ብዙ ጀግኖች እንደነበሩ አውስተዋል። ከብዙ ብዙዎቹም መካከል አንድን ጀግና ወታደር ወስደው እንዲህ አስነብበውናል።

ወታደር ደረጀ ይባላል። አንድ ወሳኝ ግዳጅ ላይ እንዳለ ትከሻውን ይቆስላል። እነሻለቃ ማሞ (ያኔ መቶ አለቃ) እንዲገለል ያግባቡታል። አሻፈረኝ ይላል። እናም ወደ ምሽጉ ገብቶ ጠላትን መፋለም ይቀጥላል። ግን ይህም አልበቃው ኖሮ ከምሽጉ ዘሎ ወጥቶ ወደ ጠላት ወረዳ ይወረወራል። ጸሃፊው እንዲህ ይገልጡታል…

“እግሩን አንፈራጦ ቆሞ ክላሺንኮቭ ጠመንጃውን ባንድ እጁ በሙሃይቱ ደግኖ ያለውን ጥይት በጠላት ላይ ያርከፈክፈው ጀመር። … እግሮቹን መሬት ላይ ቸክሎ እስከ መጨረሻው ሕቅታ መተኮሱን አላቋረጠም።.. ደረጀ እልሁንና ቁጭቱን እስከ መራራ ፍጻሜው ድረስ ለመወጣት ሲል ያደረገውን ለማመን የሚያዳግት ገድል ነበር። ጥይት ሰውነቱን እየበጣጠሰውና እየቦጫጨቀው ፍንክች ሳይል የመጨረሻውን ጥይት ተኩሶ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሬት ላይ በጀርባው ተዘረረ።” (ገጽ 155)

ከበደ ይባል የነበረው ጎበዝ መትረየስ ተኳሽና ሌሎችም ጀግኖች በስህተት ከወገን በተሰነዘረ የመድፍና የታንክ ድብደባ ማለፋቸውንም ጸሐፊው አልሸሸጉንም። ታዲያ ከበደ ቆስለ እንጂ አልሞተም ነበርና ረዳቱ ተክላይ አሟሟቱን ለሻለቃ ማሞ እንዲህ ይገልጸዋል። “… ቆስሎ ደግፈነው ስናመጣ እራሱን ይረዳ ነበር… የተራራው እናት ላይ ላይ ደርሰን ወደ እርሶ እየተቃረብን ሳለ፣ የታንኩ ድብደባ ጀመረ። ወዲያው በያገኘንበት ቋጥኝ ስር ሁላችንም ተሸሸግን። እሱ ከተከለለበት ቦታ “ዶፍ” የሚል ተኩስ ሰማን። አጠገቡ ሄጄ ሳይ የገዛ ሽጉጡን ጠጥቶ ራሱን በራሱ አጥፍቶ አገኘሁት… እኔ ጀግና ሰው ሲሞት ማየት አልፈልግም። በከበደ ፈንታ እኔው በሞትኩ!” (ገጽ 181) ሲል ለጀግና ጓደኛው ህልውና የራሱን ሕይወት ቢገብርለት እንደሚሻ ላዛዡ ገልጠላቸዋል። ድንቅ ፍቅር፣ ድንቅ የትግል ጓድነት ቋጠሮ!

ሌላው ተጠቃሽ የመትረየስ ተኳሽ ወታደር ሽመልስ ነበር። ወደ ጠላት ወረዳ ገስግሶ ሄዶ ተምራዊ ማጥቃት የፈጸመና ሊያጠቃ የመጣውን የሻቢያ ጦር ድምጥማጡን ለማጥፋት ሰበብ የሆነ ጀግና ነበር። ከጉድባ ጉድባ መትረየሱን ተሸክሞ እየተሯሯጠ በጠላት ላይ ድንገተኛ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ድልን ለወገን አጎናጸፈ። የማታ ማታም ቅንድቡ ላይ ተመቶ ይወድቃል። በላቸው የተባለው ረዳቱም ቁስሉን ቢያስርለትም ሽመልስ የሚተነፍስ አልሆነም። ሞተበት። እናም በላቸው አቃባሪ ፍለጋ ወደ ወገን ጦር ይፈጥናል። የሽመልስ አስከሬን ከነበረበት በርከት ብለው ሲመለሱ፣ የጀግናው አስከሬን ከመቃብር በታች ውሎ ያገኙታል። በዚያ ፍጥነት በማንና እንዴት ሊቀበር እንደቻለ ግራ ገብቷቸው ይመለሳሉ። አመሻሹ ላይም የጀግና ወታደራዊ ያቀባበር ሥነ ስርዓትን ያከናውኑለታል።

የሽመልስ የጀግንነት ገድል እየተወሳና እየታሰበ እያለ ከስድስት ወራት በኋላ፣ በጦር ሃይሎች ሆስፒታል ውስጥ ታዬ የሚል ዜና ይሰራጭ ጀመር። ለካስ ጓደኛው በላቸው አቃባሪ ፍለጋ ሲሄድ፣ አግላዮች ደርሰው አስከሬኑን ወደ ማግለያ ጣቢያ ወስደውት ኑሯል። ታዲያ ሌሊት ላይ ካስከሬኖቹ መሃል የኩርፊያ ድምጽ የሚያሰማ ሰው አለ የሚል ጥቆማ ከቁስለኞች ለሃኪሞች ይደርሳል። ሃኪሞቹ ሊያጣሩ ሲሄዱ እውነትም ሞተ ያሉትን ያልሞተውን ሽመልስን ያገኙታል። በማግስቱ ከሌሎች ቁስለኞች ጋር ወደ አሥመራ በሄሊኮፕተር ይላካል… ከዚያም ለከፍተኛ ሕክምና ወዳዲስ አበባ ይሸጋገራል… ከዚያም ለከፈትኛ የቀዶ ጥገና ሕክምና ወደ ምሥራቅ ጀርመን ይበራል። የሚቻለው ሁሉ ተደረገለት… ግን ተባህር ማዶ ሲመለስ፣ ያይምሮ መታወክ ሰለባ ሆኖ መቅረቱን ስንረዳ ውስጣችን በሃዘን ይረታል።

ስለ ጀግኖች የበታች ሽማምንት፥ ተራ ወታደሮች፥ መስመራዊና ከፍተኛ መኮንኖች፥ ጸሃፊው የሚነግሩንን ያህል ስላንዳንድ ጀግኖች የጦር አዛዦችም ያወሱናል። የኮሎኔል ለሜሳና የመቶ አለቃ ወጋየሁ ደግነቱ (ድምጻዊው… አፈር ይቅለለውና) የጦር ግምባር የግዳጅ አፈጻጸም ፍጥጫም ፈገግ ከማሰኘቱም ባሻገር፣ ፍጻሜው ልብን ያረካል። ጎበዝ የበላይ አካልና የጦር አዛዥ አንድን ጀግና በጭንቅ ጊዜ መውለድ እንደሚችል የኮሎኔል ለሜሳ ቁርጠኛ ወሳኔና ትእዛዝ፣ የመቶ አለቃ ወጋየሁን እንደዘፈኑ ሁሉ ጠላትን ቀርጠ ቀርጠ ለመጣል አስችሎታል… በተግባር።

የኮሎኔል ቢሹ ገብረ ተክሌ አስደናቂ የግዳጅ አፈጻጸምም በደራሲው መጽሃፍ ውስጥ ውል ያለው ተጠቃሽ ነው። እኚህ ጀግና በትውልድ ክፍለ ሃገራቸው በኤርትራ ሰላም ሳይሰፍን ጸጉራቸውን ላለመቆረጥ ለራሰቸው ቃል ገብተው ይኖሩ የነበሩ ቀራጥ ነበሩ። ኮሎኔል ቢሹ ጥይት አይመታቸውም እየተባሉ ይታመኑ የነበሩና 31ኛ ሻለቃን ከኮሎኔል ክፈተው መርኔ ጋር ነፍስ አድን ተወርዋሪ ጦር አድርገው የገነቡ ጀግና ነበሩ። ዝርዝር ገድላቸው ብዙ ብዙ ነው። የሕልፈታቸው አስዛኝነትም ያጨረውን ቁጭት ደራሲው በዝርዝር አስቀምጠውታል። በሻቢያ የተገዛችው ፍቅረኛቸው ሕይወታቸውን አስገብራቸዋለች። ታሪካቸውና ስማቸው ግን ከመቃብር በላይ ሁሌም ገኖ ይኖራል።

የብ/ጄኔራል ሣምሶን ኃይሌ ታላቅ ትእግሥትና የጄኔራል ተሰፋዬ ሃብተ ማርያም ያወቅሁሽ ናቅሁሽ እብሪት ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው የዚህ መጽሃፍ ደራሲ ነጥቦች አንዱ ነው። (ገጽ 240) በፓርቲ መዋቅር የበላይ የሆኑት ተሰፋዬ በጦር አዛዥነታቸው የበላይ የሆኑትን ጄኔራል ሣምሶንን እንዴት ባንድ ቀውጢ የግዳጅ ሰዓት ላይ እንደተፈታተኗቸው በሰፊው ገልጸዋል። ይህም ለጠሩ የዘመቻ ስኬት ምን ዓይነት ዳፋ እንደነበር ገልጸው፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ እንደ ሜ/ጄኔራል ሁሴን አህመድና ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጅማ ዓይነት በሳል የጦር መሪዎች እንዲህ ያለ አለመግባባት ባለበት ሰፍራ ላይ የተጫወቷቸውን ገንቢ ሚናዎች አካፍለውናል። በቁምነገር መሃል ፈገግ የሚያሰኙ ቀልዶችን ጣል ማድረግ የሚወዱትን የጄኔራል ሣምሶንን ስሜት በሚገባቸው ቋንቋ እየኮረኮሩ መረጋጋትን በቀውጢው ሰዓት ላይ ለማስፈን ያደርጉ የነበረው ጥረት የሚደነቅ ነበር።

የዚህ መጽሃፍ ደራሲ የዋሉባቸውን የጦር ሜዳና የሥራ አካባቢዎች ከራሳቸው ገጠመኝ አኳያ በመጻፋቸው ምክንያት ሁሉንም ጀግናና ሁኔታ በዝርዝር ማውሳት እንደማይቻላቸው ግልጽ ነው። እናም በዚህ አጋጣም የምናነሳሳቸው ሌሎች ብዙ ብዙ ጀግኖቻችንም በተለያዩ ጦር



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ግምባሮች እንደነበሩ ማስታውስ የግድ ይላል። የዚህ አስተያየት ጸሃፊ የጦር ሜዳ ጋዜጠኛ ሆኖ በዘመተበት ወቅት ያወቃቸውን አንዳንድ ጀግኖች ዛሬም በኩራት ያስታውሳቸዋል።



ሜ/ጄ. ረጋሣ ጅማ ባመራር ላይ፥ ተሰነይ 1970 ዓ.ም.

ሜጀር ጄኔራል ረጋሣ ጅማና ብርጋዴር ጄኔራል የማታ ምስክር ከብዙዎቹ ጀግና የጦር አዛዦች መካከል የሚመደቡና የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የሚያስታውሳቸው ናቸው። ጀነራል ረጋሣ ጅማ አፈር ይቅለላቸውና (ያኔ ኮሎኔል) በ1970ዓ.ም. 501ኛ ግብረ ሃይልን ይዘው በትክል ድንጋይ በኩል ወደ ኤርትራ በዘመቱበት ጊዜ፣ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የጋዜጠኞችን ቡድን እየመራ ይከተላቸው ነበር። እናም አንድ ቀን ጋሉጅን ለማጥቃት ባሰሳ መልክ ስንንቀሳቀስ፣ ገርገፍ የሚባለው ጅረት ላይ ስንደርስ፣ ጀብሃ መሽጎ ጠበቀን።

አጋጣሚ ሆኖ የጋዜጠኞቹ ቡድንና ጀነራል ረጋሣ ከግምባር ቀደሙ አሳሽ ሃይል ጋር አብረን እየተንቀሳቀስን ነበርና፣ ድንገተኛው የጠላት ጥቃት እላያችን ላይ ወደቀ። ያኔ ነበር እኚህ ቆራጥ የጦር መሪ በያዝዋት ከዘራ እየጠቆሙ "አንተ በዚያ... አንተ በዚህ ግባ..." እያሉ ጦሩን እያስተባበሩ ወደፊት ሰንጥቆ እንዲሄድ ቆራጥ አመራርን የሰጡ። ባጭር ጊዜ ውስጥ ድብልቅልቁ በወጣው ድንገቴ ውጊያ ውስጥ የወገን ጦር እየሰነጠቀ ገፍቶ ሄደ፣ ጠላትን መደመዱን ያጠፋውና ውጤት የጨበጠው በነ.ህ የቁርጥ ቀን ጀግና ነበር። በዚያ ድንገተኛ ወጊያ ጀነራል ረጋሣ ሳይደናገጡ፣ ለአንዲት መተኪያ ለሌላት ሕይወታቸው ሳይሳሱ ፊት ለፊት ጠላትን ተጋፍጠው የኔን ብጤ ሲቪል ዘማች አይረሴ ምስል



ዘጋቢው በጦር ግምባር የሬዲዮ ጋዜጠኝነት ግዳጅ ላይ፥ ተሰነይ 1970 ዓ.ም.

ውስጤ ስለውብኛል። ወርቅ ላበደረ ጠጠር ሁኖ፣ እኚህ ጀግና በዘመነ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሕይወታቸው በወህኒ ቤት አልፋለች።

ስለጀነራል የማታ ምስክርም አብረዋቸው ከነበሩ የቅርብ ጓደኞቻቸውና፣ ኮሎኔል መንግሥቱ ካሉበት ከዚምባብዌ ሆነው በካሴት ካስደመጡት ንግግራቸው ብዙ ይሰማል። ሲፎክሩ "ኢጆሌ ባሌ..." ማለት ይቀናቸው የነበሩት ጄኔራል የማታ ምስክር ሽሬ የነበረው የወገን ጦር መሪ ነበሩ። ሻለቃ ማሞ በዚህ መጽሃፋቸው ላይ እንደተረኩት ሁሉ፣ የትግራይ የበላይ አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ የነበሩት መጋቢ ሃምሳ አለቃ ለገሠ አስፋው ከንፋስ ስልክ መኖሪያ ቤታቸው ተቀምጠው፣ የትግራዩን ጦር በቀጭን ትእዛዝ (ወይም በሪሞት ኮንትሮል ልበለው?) ይመሩ ስለነበር፣ እነ ጀነራል የማታ ምስክር የሳት እራት ሊሆኑ ችለዋል። (ገጽ 350) ከነለገሠ ይሰጥ በነበረው የሚሊቴሪ ሳይንስ እውቀትን ባላወቀው ጀበደኛ አመራር የሽሬው ጦር ተፈታ። ወያኔ ከፍተኛውን የድል አክሊል ተቀዳጀ። ይህንን መራራ እውነት ባይናቸው አይተው በሕሊናቸው መቀበል ያቃታቸው ቆራጡ ጀግና ጄኔራል የማታ እስከመጨረሻው ድረስ ቆርጦ ለመዋጋታና ለማለፍ ይወስናሉ። ወጊያውን




PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በገዛ ፈቃዱ ጥሎ የሚሸሸውን ጦር በየመንገዱ እያስቆሙ፣ "ስለኢትዮጵያ አምላክ... ወድቃ ስለተነሳችው ባንዲራ... " እያሉ ውዲቱን ባንዲራ እያነጠፉ ተማጸኑ። ብዙ ብዙ ተሰፋ አስቆራጭና አሳዛኝ ምላሽ ተሰፋ ከቆረጠው ተዋጊ ጦር ተሰጣቸው። የወገንን ጦር በዚህ ዓይነት የነለገሠ አስፈው መናኛ አመራር መፈታት ካጤኑ በኋላ ነበር፣ ያቺን ውድ ባንዲራ እንደተከናነቡ፣ ጀኔራል የማታ የቴዎድሮስን ጽዋ የጨለጡት።

ጸሃፊው የግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም፥ ኩዴታ ቁንጮ ስለነበሩት ስለ ሜጀር ጀኔራል መርእድ ንጉሤ ያላቸው በጎ አመለካከት፣ ዋንጫ ሞልቶ የሚፈስ ነው። ለሜጀር ጀኔራል መርእድ ንጉሤ ልዩ አክብሮት፥ አድናቆትና አተያይ አላቸው። እንዲህ ሲሉም ይገልጿቸዋል።

"ሜጀር ጀኔራል መርእድ ንጉሤ ለሃገርና ለሕዝብ ያላቸውን ፍቅር፥ ሃቀኝነታቸውን፥ ጠንካራ አቋማቸውን፥ ጥሩ አድማጭነታቸውን፥ ታጋሽነታቸውንና መካሪነታቸውን ሳይ ከመጽሃፍ ካነበብኩትና ባፈታሪክ ሲነገር ከምሰማው በቀድሞ ዘመን ከነበሩት የኢትዮጵያ መሪዎችና አርበኞች እንጂ በዘመናችን ከሚገኘው ትውልድ ጋር የሚደመሩ አይመስለኝም ነበር።" (ገጽ 356) ሲሉ እጅግ የላቀ አድናቆታቸውን ለኚህ ስመ ጥር የጦር ገበሬ ይገልጹላቸዋል።


የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የ501ኛ ግብረ ኃይል መምሪያ

ቁጥር 1/501/ቀ/37/638
ቀን 29/12/70

ለማስታወቂያና የውርስ ብ/ጀ ሚኒስቴር

በያሉበት

ጉዳዩ፡ ስለ ምስጋና

በተለይም ይህንኑ ያልታደለ የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት ገና በጅምሩ ባጭር ያስቀሩትን ችኩሉን ጀኔራል አበራን ጸሓፊው እየኮነኑ፣ የሜጀር ጀኔራል መርድ ንጉሤንና የትግል ጓዳቸውን የብ/ጄኔራል አምሃ ደስታን የመጨረሻ የሕልፈት ምስጥር ያወሱናል። ሁለቱ ምርጥ ጀኔራሎች ሁሉም ነገር ከተበለሻሸና እጨካኙ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እጅ መግባታቸው የማይቀር መሆኑን ሲረዱ በራሳቸው ላይ የወሰዱትን እርምጃ ይተርካሉ።

የልዩ ጥበቃ ብርጌድ አሳሽ ጦር ሁለቱ የጀኔራሎች ወደ ነበሩበት ቢሮ ሲደርስ፣ ለየት ያለ ያሚሚት ሁኔታ ነበር ያስተዋለው። ሁለቱ ጀግኖች በኢትዮጵያ ባንዲራ እንደተጠቀለሉ እራሳቸውን በራሳቸው አጥፍተው ነበር ያገኙዋቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ አሥመራ ላይ በነጀኔራል ደምሴ ቡልቶ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ጭፍጨፋ እኚህ ጸሃፊ በሰላ ብእራቸው አሳምረው ገልጸውታል ። በዘመቻ መምሪያው ንቁ ባልደረብነታቸው ይደርሳቸው የነበሩትን ትኩስ መረጃዎች ተንተርሰው ያን አሰቃቂ የ102ኛ አየር ወለድ መቅሰፍት ተርከውታል። "ሠራዊቱ አዛዦቹንና ከፍተኛ መኮንኖቹን በአሰቃቂ ሁኔታ ከገደለ በኋም፣ አስከሬናቸውን በመኪና እየጎተተና አደባባይ ላይ እያነጠፈ፣ በመፈንጠዝ የአውሬነት ባህሪይ አሳይቷል።" (ገጽ 417) ሲሉ ተችተውታል። ብ/ጄኔራል ታደሰ ተሰማን እምስኪን ቤተሰቦቻቸው ፊት የረሸናቸው ያየር ወለዱ ጀብደኛ ምን ዓይነት ሕሊና እንደፈጠረበት ቆም ብሎ እራሱን ላንዲት ደቂቃ ጠይቆ ይሆን? ማለታችንም አይቀርም።

ባጠቃላይም አገሪቱ በግማሽ ምእተ ዓመት ውስጥ ካፈራቻቸው ታላላቅ የጦር ሰዎች መካከል በዚህ መፈንቅለ መንግሥት ጠሰ 39 ጀኔራል መኮንኖች፥ አንድ ሪር አድሚራል፥ አርባ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ከኮሎኔል እስከ ሻለቃ ማእርግ ያሉ ከፍተኛ መኮንኖች፥ ስድሳ አራት ከዚያ በታች ያሉ መስመራዊ መኮንኖች ማለትም በድምሩ 140 መኮንኖች ጭዳ መሆናቸውን ደራሲው አስምረውበታል።

የደርግ ነገር ሲያልቅ አያምር መሆኑን የሚተርኩልን እኚሁ መኮንን፣ የኮሎኔል መንግሥቱን አሳፋሪ ፍርጠጣ፥ የለገሠ አስፋውን ዓይነት ያህያ ነጂ ገበሬ ተማስሎ የመሰወር ሙከራ፥ የነአሥር አለቃ ግርማ አየለ (የደርግ አባል) ዓይነት የጠሩን ገንዘብ ይዞ ዓይነት ኩብለላ ሙከራና የመሳሰሉት ገጠመኞች ሁሉ በእውነታ ገጽታቸው ተስለዋል። ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ዓይነት የሆነው የደርግ ጣፋጭ የሥልጣን ጥማት ዘመን ተጅምሩ እስከ ጭርሱ በደምና በሃዘን እንደጨቀየ መፈጸሙን ሻለቃ ማሞ አድምቀው አሳይተዋል።

በኤርትራ የነበረው ያ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ጦር ተፈቶ ሲበተን፣ የደረሰው እልቂት ደሞ በውጊያ ላይ ካለቀው የላቀና የግፍ ግፍ ግፍ... በሻቢያ የተፈጸመበት እንደነበር ደራሲው በዚህ ሥራቸው ላይ እየነቀሱ አሳይተዋል። አንድ እብሪተኛ የሻቢያ ወታደር በምርኮኛው የወገን ወታደር ላይ እፊቱ ላይ ሲተፋበት፣ መደፈሩን ከሞት የቆጠረው ጀግና የሻቢያውን ወታደር የራሱን የጅ ቦምብ ነጥቆ በመወርወር ይገለውና ይበቀለዋል። ያንን ያስተዋለው ጠላት በምርኮኝነት የያዛቸውን ከአንድ ሺህ በላይ የወገን ጦር ባንድ ጉድጓድ ውስጥ ሰብስቦ፣ አሰቃቂ ጭፍጨፋ በማካሄድ ትውልድ ይቅር የማይለው ግፍ መፈጸሙን ደራሲው ገልጸዋል። ከዚህ ርሸና አምልጠዋል የተባሉትን ደግሞ የገቡበት ገብተው በመልቀም፣ ራቁታቸውን እያቆሙ ለከብት ጠባቂ እረኞች የኢላማ ተኩስ መለማመጃ እንዳደረጉዋቸው የዘመቻ መምሪያው አንጋፋ መኮንን ሻለቃ ማሞ በቁጭት ይገልጹታል። ድርጊቱ ከዓለም አቀፍ የምርኮኛ አያያዝ ሕግ ውጭ የተፈጸመ የጦር ወንጀለኝነት እንደሆነም አመልክተዋል። (ገጽ 473) እነ አይተ ኢሳይያስ አፈወርቂ የነሚሎሶቪችን፥ የነቻርለስ ቴይለርንና የነአልበሽርን ዓለም አቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል ችሎት የማይጎበኙበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለ ማስተዋል የሚያዳግት አይመስልም።

ኤርትራ ውስጥ ከመደበኛ ጦርነቱ ውጭ ደም በጠማቸው የሻቢያና የጀብሃ አውሬዎች ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ ያለቁት ምርኮኞች ታሪክ እጅግ የሚዘግንን ነው። የኢዲዩ ታጋይ የነበሩት ግደይ ባሕሪሹም "እሞራው" በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ የገለጹትን ያይን ምስክርነት ያነበበ ሁሉ፣ ያንን ትውልድ አሰጠያቂ የሻቢያና የጀብሃ የግፍ ግፍ በዝርዝር ማስተዋል ይችላል። በሣህል በረሃ ውስጥ የታገቱ ምርኮኛ ወታደሮች በቁማቸው እንዴት የሞትን ሞት ባንድ ምሽግ ውስጥ ቁጭ ብለው እንደሚያስተናግዱት ደራሲው አሳምረው ገልጸውታል። መጀመሪያ ያለ ምግብና ውሃ የቀን ሃሩርና የሌሊት ቁር የሰውን ልጅ ለሳምንታት ብሎም ለወራት በቁሙ በልቶት ይጨርሰዋል። ይህም ሂደት አለው። ያልታደለው ምርኮኛ በቁም እንደጨው እየሟሟ መሄዱ በየቀኑ ይቀጥላል። ቀጥሎም ነፍስ ሳትወጣ ጆሬ አሞራ እየመጣ አይንን አስቀድሞ መጓጎጥ ይጀምራል። እራሱን ካሞራው መከላከል የማይችለው በሞት አፋፍ ላይ የሚገኘው ምርኮኛ በቁሙ እንዲህ እየተበላ ወደ መጨረሻው በድንነት ይሸጋገራል። አጠገቡ ተኝቶ እለተ ሞቱን የሚጠባበቀው ሌላው ምርኮኛ ወገኑ ሁሉ፤ የሟች ጓዱን አስከሬን መቅበር ወይም ማግለል አቅቶት፣ ናላን የሚያዞረውን የተበላሸ አስከሬን ሽታ እየታጠኑ እሱም ፈጣን የሞት ጥሪውን እያቃሰተ ይጠባበቃል። እናም በዚያች የኤርትራ ምድር ላይ የታየው ግፍ ተሰፍሮ ተሰፍሮ የማያልቅ ነውና ለተጨማሪ ትኳሬ "እሞራው"ን አፈላልጎ ማንበቡ ከተራ ፕሮፖጋንዳ የራቀ ጥሩ ግንዛቤን ያስጨብጣል።

የዚህ መጣጥፍ አቅራቢም ያይን ምስክር የነበረበትን አንድ አሰቃቂ የጅምላ ጭፍጨፋ ታሪክ ሁሌም ያስታውሳል። 501ኛው ግብረ ሃይል የጀብሃን ወንበዴ እንደ ቅጠል አርግፎ በ1970 ዓ.ም ሀምሌ ወር ላይ ተሰነይን ሲቆጣጠር፣ የጠበቀን መርዶ ቀላል አልነበረም። እንደ ነገ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አሊጊደርን አጥቅተን ልንይዝ ስንዘጋጅ፣ ሌሊቱን ጀብሃ ለሰባት ዓመታት ያህል አስሮ በረሃብና በከባድ ሥራ ያሰቃያቸው የነበሩትን 300 የወገን ጦር ምርኮኞችን እጅግ አረመኔያዊ በሆነ መንገድ፣ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ፈጽሞባቸው ነበር የፈረጠጠው። ሁለት በተአምር ከጅማላው ጭፍጨፋ ያመለጡ ወታደሮች ከአስራ አምስት ቀናት የረሃብ፥ የጥማትና የእንግልት  የኤሊ ጉዞ በኋላ የወገን ጦር ወዳለበት ወደ ተሰነይ መጥተው (15 ኪ.ሜ. በአስራ አምስት ቀን!!!) ሊያረዱን የቻሉት። በሥፍራው ለነበርነው ጋዜጠኞችም ዝርዝር ሁኔታውን የገለጹልን እንዲህ እያሉ ነበር።

"ምሽቱን  ከታጎርንበት የቆርቆሮ መጋዘን ቤት መጡና፣ የወገኖቻችሁ ጦር ስለመጣ ልናስረክባችሁ ፈልገናልና ቶሎ ቶሎ ጓዛችሁን ሸክፉና በሰልፍ ውጡ አሉን። እውነት መስሎን እንደ ባልዲጃ አድርገን የምንጠቀምበትን የሰሌን አቁማዳችንን በየትከሻን አንግበን፣ በአጋም እሾህ የታጠረውን ግቢ ልንወጣ ስንል አንድ ትእዛዝ ሰጡን። በረባሶ ጫማችሁን በሙሉ አውልቁና አስቀምጡ አሉን። ምክንያቱ ባይገባንም ወደ ወገኖቻችን የምንሄድ በመሆናችን ባዶ እግር መቅረታችን ቅር ሳይለን አወለቅንናወደ መሩን ተጓዝን። ከዚያም ባራቶሎ የተባለው ኢጣሊያናዊ ከበርቴ አሊጊደር ላይ ለጥጥ መስኖ ልማቱ ውሃ ለመሳብ ወዳስቆፈረው ሰፊና ጥልቅ ቦይ (ካናል) እንደተሰለፍን አስገቡን። ከዚያም በረድፍ አስገብተውን ሲጨርሱ፣ ከቦዩ አፋፍ ላይ ሆነው ከበቡንና በመትረየስ ከግራን ከቀኝ አጨዱን። ዋይታና እሪታው ላንዲት ቅስበት ብቻ ነበር። በየወድቅንበት አሸለብን። ግን በዚህ አላበቁም። ነፍሱ ያልወጣችውን እየመረመሩ በማጣሪያ ተኩስ አጠናቀቁን። አሁንም ደሞ አላበቁም። ቤንዚን አመጡና ከዳር እዳ በላያችን ላይ ካርከፈከፉ በኋላ እሳት ለቀውብን እየፎከሩና እየተሳሳቁ ጥለውን ሄዱ። ሁለታችን በወታደራዊ ስልት የሞትን መስለን እርስችንን በመደበቅ አንዳችን ቆስለን አንዳችን ምንም ጥይት ሳይነካን ነፍሳችንንማትረፍ ችለናል።" ነበር ያሉን።

በኮሎኔል ረጋሣ ጅማ ትእዛዝ፣ የጋዜጠኞቹ ቡድን (እኔ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ፥ የመ/አለቃ አበራ ፋጡሌ ቪዲዮ ቀራጭ ከመከላከያ፥ ያሥር አለቃ እንግዳ ፎቶ ግራፍ አንሺ ከመከላከያ፥ በኋላ ግዳጅ ላይ እያለ በሄሊኮፕተር አደጋ የተሰዋ) ይህ አሳዛኝና የፈሪ በትር ጭፍጨፋ ወደ ተፈጸመበት የመስኖው ጥልቅና ሰፊ ቦይ አንድ የመቶ ጦርና ሁለቱን በሕይወት የተረፉትን ምርኮኞች ይዘን ተጓዝን። ለማየትም ለመጠጋትም የሚዘገንንና የሚቀፍ አሰቃቂ ትእይንት ነበር የጠበቀን። ምርኮኞቹ በእሳት ተንጨርጭረው አረው ከሰለው ዶግ አመድ ሆነው ነበር ያለፉት። ከጥይቱ ይልቅ እሳቱ ይበልጥ እንደጎዳቸው ከሚታየው ያካል እንቅስቃሴ ገጽታ ማስተዋል ይቻል ነበር። ሁላችንም የምናየውን ማመን ተስኖን በእምባና በብስጭት የውስጣችንን ስሜት ለመግለጽ ታገልን። ግን ከቶም ከቶም ሊወጣልን አልቻለም። ዛሬም ድረስ ያ አሰቃቂ ትእይንት እየተመላለሰ የሕሊናዬን ጓዳ ያንኳኳል።

ምርኮኞችን በንዲህ ዓይነት መንገድ ከሚያሰተናግድ አረመኔ ጠላት ጋር ነበር ያ የወገን ጦር ከሠላሣ ዓመታት በላይ በኤርትራ በረሃ ውስጥ ሲቃጠል የኖረው። እንዳቅምቲ ከሦስት ወራት በላይ የቃረምኳቸው የጦር ግምባር ትዝታዎቼ የኪስ ማስታወሻ ግዳጇን ፈጽሜ ልመለስ ጥቂት ቀናት ሲቀሩኝ ባልታወቀ ሰዎችና ዘዴ ተመንትፎብኛል። የሰረቀኝን ነፍሱን አይማረውና የጦር ግምባር የየእለቱን ዝርዝር ሁኔታ እመዘግብበት የነበረኝ እንደጠፋ ቀርቷል። ለነገሩ እንኳን በሱ ያለፈልህ ነበር ያሉኝ ደጉና ርህሩሁ የያኔው ኮሎኔል የኋላው ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጅማ። ይቺ የማጽናኛ ቃላቸው የዋዛ አልነበረችም። ከወታደራዊ የደህንነት ክፍሉ ያገኙት ጥቆማ በሕይወቴ የመጣ ጉዳይ ነበርና ነው። ወዳጅና ጠላት ባለየበትና አንዳንዴም ተመሳሰሎው ባየለበት ሠዓትና ስፍራ ድንገት ሰለባ መሆንም አለ። የሚዲያን ኃያልነት አንግቦ፣ በጦር ሜዳ ላይ መገዘጥ የልማት ዜናን እንደመሥራት የሚቀል አይደለም። አንድ የኦፐሬሽን ስህተት ተፈጽሞ ጉዳት በደረሰ ቁጥር፣ ጋዜጠኛውም "ለምን ይህ ውጊያ ውጤቱ የተበላሸ ሆነ?" ብሎ መጠየቁን አይተው፤ መላሹም ይህን ዜና ለበላይ በላይ ልኮ ሊያስጨልፈኝ ነው ብሎ መስጋቱን አይተው!... ተጠያቂው መላሸ የክፍለ ጦር፥ ያለያም የብርጌድ፥ ያለያም የሻለቃ፥ ያለያም የሻምበል፥ ያለያም የመቶ ጦር አዛዥ ሊሆን ይችላል። ከጥይት ባርቆ ነው ዓይነት



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

*የግድያ ሴራ በጊዜ ነቅተው ነፍሴን የታደጉትን ሜ/ጄኔራል ረጋሣ ጅማን ሁሌም ሳመሰግናቸው እኖራለሁ። ላንድ ወር ያህል የሌሊት መኝታዬን አድራሻ ከብርጌድ ብርጌድ እየቀያየርኩ አይፋና ዚል ስር ተድብቆ መተኛት ከሳቸው በምስጢር የተሰጠኝ አባታዊ መመሪያ ነበር። ተጠቀምኩበት። እናም አመለጥኩበት። አንድ ቀን ዝርዝሩን የማቀርብበትንም አጋጣሚ እናፍቃለሁ።*

*አሁን ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳዬ ልመለስ። ከሻለቃ ማሞ ሥራ ጋር መልሼም ላጨባብጣችሁ። "እናም በ*1982/1983 *ዓ.ም. ከዚያ ሁሉ ርሸና፥ ስደትና እንክርት ተርፎ ወደ መሃል አገር የተመለሰው ሠራዊት የት ገባ? ምንስ ዓይነት አቀባበል ጠበቀው?" ብለን ደሞ ጓዳችንን መፈትሽ የግድ ይለናል። መተኪያ ለሌላት እናት አገር ብሄራዊ አንድነትና ልእልና ሲታገል ቆይቶ ባመራር እጦት ምክንያት ሽንፈትን ተቀብሎ ወደ መሃል አገር የተመለሰው ሠራዊት የሚቀበለውም የሚያስተናግደውም ወገን አልነበረውም። ይልቅስ በወያኔ/ኢሕአዴግ ሌላ አዲስ አጠራር ተነጉቶለት "የደርግ ወታደር" በሚል ቅጽል ስም ተገፋ፥ ፊት ተነሳ፥ ተሰቃዬ። ከቤት ከንብረቱ ተፈናቅሎ እንደወጣ ቀረ። በወገኖቹ ፊት ተዋርደ፥ በእናት አገሩ ምድር እምብርት ላይ ተቀመጠ፤ የላስቲክ ቤት ኑሮ እንኳን አጥጦበት ያላንዳች መጠለያ ክረምት ከበጋን አስተናገደ። የጀግናው ሚሊሺያ አሊ በርኬ አይነት ብርቅ ልጆች በእስር፥ በልመናና በጎዳና ተዳዳሪነት ብዙ ተሰቃይተዋል። ሻለቃ ማሞም በዚህ በሳል ሥራቸው ውስጥ ይህን ጉዳይ ሳሳ ባለ መልኩ ማመልከታቸው አልቀረም። ሆኖም ወያኔ/ኢሕአዴግ ነባሩን የኢትዮጵያን ሠራዊት አዲስ አበባ ጎዳና ላይ ለማኝ ስለማድረጉ ብዙ ሊሉን የሚችሉበት ነጥብ ነበራቸው እንላለን። ይህም ለፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታው ሳይሆን በኢልቦለድ ጠባዩ እውነትን ስለ እውነት መመስከር ግድ ስለሚል ነው። ኢልቦለድ አካፋን አካፋ፥ ዶማን ዶማ እንዲል ቀደም ሲል መግቢያው ላይ ያመለከትነው ለዚህ ስንል ነው። እናም ሻለቃ ካስተዋሉትና ከተገነዘቡት ልምዳቸው በመነሳት በዚህና በመሰል ነጥቦች ዙሪያ ቀጣይ ሥራቸውን ሳንናፍቅ አንቀርም።*

*አሁን መጣጥፌን ልቋጭ ነው። ስቋጭ ደሞ የሻለቃ ማሞን የሥራቸውን ማጠንጠኛ አንድ ድንቅ ሃረግ እዋሳቸዋለሁ። "ጦርነትና የአእምሮ ቅርስ" ከሚለው ንኡስ ርእስ ውስጥ የጠቀሳል።*

*""...በፍልሚያ አውድማ እየተዋጉና የሞትን ጠረን እያሸተቱ ማለፍ ለጊዜው ባይታወቅም፣ ካለፈ በኋላ ግን ስለ ጦርነት ባሰቡ ጊዜ ያ የሞት ጠረን ያ የአስከሬን ክርፋት በአፍና ባፍንጫ ይገባና መድረሻ ያሳጣል። ናላ ያዞራል... ያኔም ሕይወት ህልም ወይም ቅዠት ትሆንበታለች..." ሲሉ ሰቆቃውን ገልጸውታል። እኛም እሳቸውና እሳቸውን የመሳሰሉ የጦር ገበሬዎች በእንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ትዝታ ውስጥ ሕይወታቸው ተቀስፈ እንደምትቃትት ለመረዳት አያዳግተንም። ጽናቱን ከመመኘት በላይ ግን፣ ምን ማለት ይቻለናል? ምንም! ምንም! "ኦሮማይ!..." ነው ያለው ጋሽ በዓሉ? አዎን አበቃ፥ አለቀ፥ ደቀቀ።*

ablemma@gmail.com



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com